የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COMMISSION

# በ2013 ዓ.ም. ሀገራዊ ምርጫ ድምጽ መስጫ ቀን የተደረገ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ክትትል

# ቀዳሚ ሪፖርት

## አንኳርና ምክረ ሃሳብ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) ለሀገራዊ ምርጫ 2013 ዓ.ም. ባለ6 ነጥብ የሰብአዊ መብቶች አጀንዳ ይፋ በማድረግና ለሰብአዊ መብቶች ትኩረት እንዲሰጥ ከመወትወት በተጨማሪ፤ በቅድመ ምርጫውና በምርጫው ቀን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ክትትል ሲያከናውን ቆይቷል።

ኮሚሽኑ ከሰኔ 12 ቀን እስከ ሰኔ 16 ቀን 2013 ድረስ ምርጫ በተካሄደባቸው በሁሉም ክልሎች በሚገኙ የተመረጡ አካባቢዎች ተንቀሳቃሽ የክትትል ቡድን በማሰማራት ክትትል አድርጓል። ለክትትል ስራው እያንዳንዳቸው ከ 2 እስከ 3 ባለሙያዎችን ድረስ የያዙ የክትትል ቡድኖች ተዋቅረው፣ በአጠቃላይ 94 ባለሙያዎችን የያዙ 35 የክትትል ቡድኖች በማሰማራት አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርን ጨምሮ ምርጫው በተካሄደባቸው 7 ክልሎች በሚገኙ 99 ምርጫ ክልሎች እና 404 ምርጫ ጣቢያዎች ላይ ክትትል ተደርጓል።

ምርጫው የተካሄደበት አውድ በሀገር ውስጥ የተደራረቡ ችግሮች የገጠሙበት፤ በትግራይ ክልል የተከሰተውን ግጭት ጨምሮ በሌሎችም አካባቢዎች የተከሰቱ ግጭቶች ለሕይወት መጥፋት፣ የአካል ጉዳት፣ የንብረት ውድመትና ከፍተኛ መፈናቀል ባስከተለበት፣ የተወሰኑ የፖለቲካ ቡድኖች እራሳቸውን ከምርጫው ሂደት ባገለሉበት፣ የተወሰኑ የፖለቲካ ቡድን አመራሮች በእስር በሚገኙበት ወቅት መሆኑ የማይዘነጋና ከግምት ውስጥ የሚገባ ተግዳሮት ነው።

ይህ ሀገራዊ ተግዳሮት እንዳለ ሆኖ፤ ኢሰመኮ በምርጫው መዳረሻ ቀናት እና በምርጫው እለት ክትትል ባደረገባቸው አካባቢዎች የተወሰኑ የሰብአዊ መብቶች አጠባበቅ ክፍተት የታየ ቢሆንም፤ በአብዛኛዎቹ ቦታዎች የጎላ ወይም የተስፋፋ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት አልነበረም። እንዲሁም ኢሰመኮ ክትትል ባደረገባቸው በአብዛኛዎቹ አካባቢዎች የምርጫው ዕለት ሂደት ያለ የጎላ ችግር በሰላም ተጀምሮ በሰላም የተጠናቀቀ በመሆኑ፤ የምርጫው ዕለት ሂደት ሰላማዊ፣ ሥርዓትን የተከተለና በአብዛኛው ሁኔታ ሰብአዊ መብቶች የተከበሩበትና በብዙ መልኩ የተሳካ የድምጽ አሰጣጥ ሂደት ነበር።

ዜጎች በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠውን የመምረጥ እና የመመረጥ መብት ለመተግበር ከንጋት እስከ ምሽት በረዥም ሰልፎች ቆመው ውለው፤ በአብዛኛው ሥነ ሥርዓት በተሞላውና ሰላማዊ በሆነ መንግድ በምርጫው መሳተፋቸው የሚመሰገን የዜግነት ኃላፊነት ተግባር ነበር። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እና የምርጫ አስፈጻሚዎች በዚህ ውስብስብ ወቅት እጅግ ውስብስብ የሆነውን የድምጽ አሰጣጥ ሂደት በተሳካ ሁኔታ መምራታቸው ሌላው የሚመሰገን ተግባር ሲሆን፣ ቦርዱ ቀሪዎቹን ስራዎችም በተገቢው ደረጃና ነጻነት እንደሚያከናውን ኮሚሽኑ ተስፋ ያደርጋል። በምርጫው ሂደት የተሳተፉ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችና ሌሎችም የምርጫው ሂደት ታዛቢዎች፣ ሚዲያዎች እና አብዛኛው የሕግ አስከባሪ አካላት በምርጫው ዕለት የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ በሰላም እንዲጠናቀቅ ያደረጉት አስተዋጾም በተመሳሳይ መንገድ የሚመሰገን የዜግነት ኃላፊነት ሲሆን፤ በቀሪው ሂደትም በሕጋዊና ሰብአዊ መብቶችን ባከበረ መንገድ እንዲቀጥሉ በድጋሚ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

እነዚህ አወንታዊና አበረታች እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በአንጻሩ በአንዳንድ የምርጫ ክልሎች ከምርጫው እለት ጥቂት ቀናት በፊት፣ በምርጫው እለትና ከምርጫው ቀን በኋላ የደረሱ የሰው ሕይወት መጥፋትና የአካል ጉዳት መድረስ ሁኔታ፣ ተገቢ ያልሆነ እስር፣ በመራጮች ላይ የደረሰ ማስፈራራት፣ በምርጫ ታዛቢዎችና ጋዜጠኞች ላይ ስለደረሰ መጉላላትና ማዋከብ፣ የምርጫው

ሂደት ለአካል ጉዳተኛ ሰዎች ያለው ተደራሽነት እና የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን የተሳትፎ መጠን በሚመለከት ይህን የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት እያቀረበ፤ የሚከተሉትን ጥሪዎች ያስተላልፋል፦

- በተለይ በኦሮሚያ፣ በአማራ እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል በተፎካካሪ ፓርቲዎች እጩዎች፣ አባላትና ደጋፊዎች ላይ እንዲሁም በፀጥታ ኃይሎች እና በምርጫ አስፈጻሚዎች ላይ ጥቃት የፈጸሙ፣ ግድያና የአካል ጉዳት፣ እስርና እንግልት ያደረሱ ሰዎች ላይ ሁሉ በአፋጣኝ ምርመራ በማድረግ ተጠያቂነታቸው እንዲረጋገጥ ፣
- የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን በሕግ የተሰጠውን በምርጫ ወቅት የሰብአዊ መብቶች ክትትል የማድረግ ኃላፊነቱንና ተግባሩን በአግባቡ እንዳይወጣ የሚያግዱ፣ የሚገድቡ ወይም የሚያሰናክሉ ሁኔታዎች በተለይም የምርጫ ጣቢዎችን ያለ እንቅፋት የመጎብኘት አስፈላጊነት እና ማናቸውም የእስር ቦታዎችን ያለ ቅድሚያ ማስታወቂያ የመጎብኘት አስፈላጊነት በሚመለከት ለወደፊቱ በማናቸውም አይነት እንቅፋቶች ምክንያት እንዳይከሰቱ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ተገቢውን እርምጃ እንዲወስዱና ሁሉም ሰዎችና ተቋማት ለኮሚሽኑ ስራ የመተባበር ግዴታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ እናሳስባለን።

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) በቅድመ ምርጫው፣ በምርጫው ቀን እና በድኅረ ምርጫ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ክትትል ሲያከናውን ቆይቷል። በተለይም ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ፣ የመዘዋወር፣ የመሰብሰብ እና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብቶችን በተመለከተ እና የሴቶችን ተሳትፎ ማሳደግ እንዲሁም ምርጫው የአካል ጉዳተኞችን እና የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ያሳተፈና ለእነሱ ተደራሽ የሆነ በማድረግ ረገድ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ክትትል ሲያደርግ ቆይቷል። ስለሆነም፣ ከሰኔ 12 ቀን እስከ ሰኔ 16 ቀን 2013 ድረስ ምርጫ በተካሄደባቸው በሁሉም ክልሎች በሚገኙ የተመረጡ አካባቢዎች ተንቀሳቃሽ የክትትል ቡድን በማሰማራት ክትትል አድርጓል።

ለክትትል ስራው እያንዳንዳቸው ከ 2 እስከ 3 ባለሙያዎችን ድረስ የያዙ የክትትል ቡድኖች የተዋቀሩ ሲሆን በአጠቃላይ 94 ባለሙያዎችን የያዙ 35 የክትትል ቡድኖች ተሰማርተዋል። ክትትሉ አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርን ጨምሮ ምርጫው በተካሄደባቸው 7 ክልሎች በሚገኙ 99 ምርጫ ክልሎች እና 404 ምርጫ ጣቢያዎች ላይ የተካሄደ ነው። ክትትል የተደረገባቸው ስፍራዎች እና የተጎበኙ ጣቢያዎች ቁጥር ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪነት ተያይዟል።

የኮሚሽኑ ባለሙያዎች በተሰማሩባቸው ስፍራዎች በሚገኙ የምርጫ ጣቢያዎች በአካል በመገኘት ምልከታ አድርገዋል፤ መራጮችን፣ የምርጫ አስፈጻሚዎችን ፣ የፀጥታ አካላትን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችን እጩዎችን፣ ተወካዮችን፣ ታዛቢዎችን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን በማነጋገር መረጃዎችን አሰባስበዋል። ከምርጫው ጋር በተገናኘ ምክንያት የተያዙ እና ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ስለመኖራቸው ለማረጋገጥ ፖሊስ ጣቢያዎችን እና የሕክምና ተቋማትን በመጎብኘት መረጃዎችን አሰባስበዋል። በተጨማሪም በተለይ በምርጫው እለት ከተለያዩ አካባቢዎች በኮሚሽኑ ነፃ የስልክ መስመር 7307 ላይ ጥቆማዎችን እና መረጃዎችን ተቀብሏል። በዚህ ረገድ ኮሚሽኑ ክትትል ባደረገባቸው በአብዛኛዎቹ አካባቢዎች የክልል እና የከተማ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤቶች፣ የምርጫ ክልል አስፈጻሚዎች እና የምርጫ ጣቢያ አስፈጻሚዎች ኮሚሽኑ ለሚያከናውነው የሰብአዊ መብቶች ክትትል ስራ አስፈላጊውን ትብብር አድርገዋል።

ይሁንና ኮሚሽኑ በምርጫ ወቅት የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ክትትል ለማድረግ በተዘጋጀበትና በተንቀሳቀሰበት ወቅት ችግሮች ገጥመውታል። በቀዳሚነት፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ

ለኢሰመኮ የሰብአዊ መብቶች ክትትል ባለሙያዎች ወደ ምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ለመግባት የሚያስችላቸውን ካርድ (ባጅ) ለመስጠት ፍቃደኛ ባለመሆኑ፣ በአንዳንድ አካባቢዎች የኮሚሽኑ ባለሙያዎች ወደ ምርጫ ጣቢያዎች ገብተው ክትትል ለማድረግ አልቻሉም፡፡

ይሁንና ኮሚሽኑ ክትትል ባደረገባቸው በአብዛኛዎቹ አካባቢዎች የክልል እና የከተማ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤቶች፣ የምርጫ ክልል አስፈጻሚዎች እና የምርጫ ጣቢያ አስፈጻሚዎች እንዲሁም የጸጥታ አካላት ኮሚሽኑ በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነት በመገንዘብና በሕግ የተጣለባቸውን ለኮሚሽኑ ስራ የመተባበር ግዴታም በመረዳት፣ ኮሚሽኑ ለሚያከናውነው የክትትል ስራ አስፈላጊውን ትብብር በማድረጋቸው፤ ኮሚሽኑን በስራው ሂደት ያጋጠመው ችግሮች እንደተጠበቁ ሁነው፤ የክትትሉን ስራ ለማከናወን ተችሏል፡፡

ኮሚሽኑ ከገጠሙት ችግሮች ውስጥ ለምሳሌ በጭሮ ከተማ በምርጫ ጣቢያዎች የተመደቡት የፀጥታ አካላት ወደ ምርጫ ጣቢያ መግባት ከልክለዋል፤ በወሊሶ ከተማ የከተማው አስተዳደር አካላት ኮሚሽኑ የክትትል ስራውን እንዳይሰራ ከመከልከል በተጨማሪ የትኛውም ምርጫ ጣቢያ እንዳይገቡ የሚል ትእዛዝ ለፀጥታ አካላት አስተላልፈዋል፤ በምዕራብ ሸዋ ዞን የፖሊስ ጽ/ቤት ሰራተኞች መረጃ ለመስጠት ፍቃደኛ ካለመሆናቸውም በተጨማሪ በዚሁ ዞን የሚገኘው የቶኬ ኩታዬ ወረዳ ፖሊስ አዛዥ ከምርጫው ቀን በፊት የኮሚሽኑ ባለሙያዎች ከወንጀል ምርመራ ክፍል እና ከተጠርጣሪዎች መረጃ እየወሰዱ በነበሩበት ወቅት ከፍተኛ ቁጣ እና ዛቻ በማሰማት የኮሚሽኑን የምርመራ ስራ እንዲቋረጥ አድርገው ባለሙያዎቹን ከፖሊስ ጽ/ ቤቱ ግቢ  እንዲባረሩ አድርገዋል፡፡

ይህ ቀዳሚ ሪፖርት ኮሚሽኑ ከሰኔ 12 እስከ ሰኔ 16 ቀን 2013 ዓ.ም. ድረስ በጎበኛቸው የምርጫ ክልሎች እና ጣቢያዎች እና በተለይም ትኩረት ሰጥቶ ክትትል ባደረገባቸው የሰብአዊ መብቶች ላይ የተወሰነ ሲሆን፣ በቅድመ ምርጫ እና በድኅረ ምርጫ ያከናወናቸውን አጠቃላይ የክትትል ተግባራትን ጨምሮ የደረሱትን አቤቱታዎች እና ጥቆማዎች እንዲሁም የምርጫውን ሂደት በተመለከተ የደረሰባቸውን ግኝቶች ያካተተ ዝርዝር ሪፖርት የማጠናቀር ስራው እንደተጠናቀቀ ይፋ የሚደረግ ይሆናል፡፡

## 1. ግድያ እና አካል ጉዳት

በተፎካካሪ ፓርቲ አባላቶች እና ደጋፊዎች ላይ ግድያ፣ ድብደባ እና የአካል ጉዳት ደርሷል፡፡ ለምሳሌ በአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) እና ኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) አባላቶች ላይ፣ በአማራ ክልል፣ ምስራቅ ጎጃም ዞን በሚገኙት ባሶ ሊበን፣ ጎንቻ እና ደምበጫ ዙሪያ ወረዳ ገሊላ ቀበሌ ላይ ድብደባ መድረሱን ለኮሚሽኑ አሳውቀዋል፡፡

በተወሰኑ አካባቢዎች የኮሚሽኑ ባለሙያዎች ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች አነጋግረዋል፡፡ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል፣ በኮንሶ ዞን፣ ጃርሶ ቀበሌ የሚኖር የኢዜማ ደጋፊ የቀበሌው 2 ሚሊሻዎች ሰኔ 12 ቀን 2013 ዓ.ም. ይዘውት ድብደባ ከፈጸሙበት በኋላ በቀበሌው ግቢ ውስጥ

ጥለውት መሄዳቸውን እና በዚያው ማደሩን፤ በማግስቱ ሰዎች አንስተው ወደ ጤና ተቋም እንደወሰዱት አስረድቷል፡፡

በኦሮሚያ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች በመንግስት አስተዳደር አካላት እና በምርጫ አስፈጻሚዎች ላይ የታጠቁ ቡድኖች ግድያ እና የአካል ጉዳት ማድረሳቸውን ኮሚሽኑ ተረድቷል፡፡ በምዕራብ አርሲ ዞን ሲበን አረሲ ወረዳ ለምርጫ ስራ ከወረዳው ተመድበው የነበሩት የወረዳው ትምህርት ቢሮ ምክትል ኃላፊ ሰኔ 9 ቀን 2013 ዓ.ም. ባልታወቁ ሰዎች ተገድለው ተገኝተዋል፡፡ በነቀምት ዲጋ ወረዳ በሬዳ ሶሮማ ቀበሌ ሰኔ 12 ቀን 2013 ዓ.ም. ከሌሊቱ 6፡00 ሰዓት ላይ የምርጫ ጣቢያ ሲጠብቁ የነበሩ 4 ሰዎች ላይ ጥቃት የተፈጸመ ሲሆን፣ የአንድ ሰው ሕይወት ሲያልፍ ሦስቱ መቁሰላቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በቡሌ ሆራ ዙሪያ ወረዳ ምርጫ ጣቢያ የዱግዳ ዳዋ ወረዳ ፀጥታ ጽ/ቤት ኃላፊ እና የቀድሞ የሙሪቲ ቀበሌ ሊቀመንበር ሰኔ 11 ቀን 2013 ዓ.ም. በታጠቁ ሰዎች መገደላቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

## 2. እስር

በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት አባሎቻቸው እና ደጋፊዎቻቸው ያለአግባብ እንደታሰሩባቸው የገለጹ የተፎካካሪ ፓርቲዎች ተወካዮች ነበሩ፡፡ ኮሚሽኑ ክትትል ባደረገባቸው አብዛኛዎቹ አካባቢዎች በምርጫው መዳረሻ ቀናት እና በምርጫው እለት መጠነ ሰፊ ወይም በብዙ ቦታዎች የተስፋፋ እስር ያልነበረ ቢሆንም በተወሰኑ ቦታዎች ሕጋዊ ያልሆነ እስር መፈጸሙን ተመልክቷል፡፡

ለምሳሌ በቤኒንሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ አሶሳ ዞን በሚገኙ የተለያዩ ፖሊስ ጣቢያዎች ውስጥ የቤንሻንጉል ህዝቦች ነጻነት ንቅናቄ (ቤህነን) ተቀማጭ እና ተንቀሳቃሽ ወኪሎች እና የፓርቲውን አመራሮች ጨምሮ 72 ሰዎች ታስረው እንደነበረና፣ የክልሉ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ከክልሉ መንግስት ከፍተኛ አመራሮች ጋር ስለጉዳዩ ባደረገው ንግግር ሁላቸውም ሰኔ 13 ቀን 2013 ዓ.ም ምሽት ጀምሮ ባለው ጊዜ ከእስር መለቀቃቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በደ/ብ/ብ/ሕ ክልል ኮንሶ ዞን፣ ኢሰመኮ በፖሊስ ጣቢያ ተገኝቶ ያነጋገራቸው 17 የኢዜማ ደጋፊዎች እና አባላት፣ ሰኔ 6 ቀን 2013 ዓ.ም. በካማሌ ቀበሌ የምርጫ ቅስቀሳ አድርገው ሲመለሱ በክልሉ ልዩ ኃይል ፖሊስ ተይዘው መታሰራቸውን አስረድተዋል፡፡ ፖሊስ ለፍርድ ቤት ያቀረበውን የጊዜ ቀጠሮ ጥያቄ ፍርድ ቤቱ ውድቅ አድርጎ በገንዘብ ዋስትና እንዲፈቱ የወሰነ ቢሆንም ፖሊስ በእስር እንዳቆያቸው ገልጸዋል፡፡ ኮሚሽኑ ባደረገው አፋጣኝ ክትትል፣ የፍርድ ቤት ትእዛዝ እንዲከበር የሚመለከታቸውን አካላት በማነጋገር ከሕግ አግባብ ውጪ በእስር ላይ የቆዩት ግለሰቦች ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም. ከጠዋቱ 1፡00 ሰዓት ላይ ከእስር ተለቅቀዋል፡፡

በዚሁ በኮንሶ ዞን ከምርጫው ጥቂት ቀናት በፊት በካራት ከተማ እና ካራት ዙሪያ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ የታሰሩ ተጠርጣሪዎች በመራጭነት ተመዝግበው ለመምረጥ ከተዘጋጁ በኋላ ከምርጫው ቀን በፊት መታሰራቸው የምርጫ መብታቸውን ለማሳጣት ተብሎ የተደረገ መሆኑና ቢያንስ የምርጫ ድምጻቸውን የሚሰጡበት ሁኔታ እንዲመቻች ለኢሰመኮ ባለሙያዎች አመልክተው ነበር፡፡ ኮሚሽኑም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ከደቡብ ክልል ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት እና ከኮንሶ ዞን አስተዳዳር ጽ/ቤት እንዲሁም የፖሊስ መምሪያ ጋር ውይይት በማድረግ 27 እስረኞች በፖሊስ ታጅበው በየተመዘገቡባቸው 11 የተለያዩ ምርጫ ጣብያዎች በመገኘት በምርጫው ተሳትፈው እንዲመለሱ ተደርጓል፡፡ በዚህ ረገድ፣ በእስር ላይ የነበሩ ሆኖም በመራጭነት ተመዝግበው የነበሩና የመምረጥ

መብታቸው በሕግ ያልተነፈጉ ሰዎችን የመምረጥ መብት ለማረጋገጥ የአካባቢው ኃላፊዎች የወሰዱት አዎንታዊ እርምጃ በጥሩ ምሳሌነት የሚጠቀስ ነው።

ኮሚሽኑ ክትትል ባደረገባቸው አካባቢዎች ከምርጫ ጋር በተያያዘ ወንጀል ተጠርጥረው የታሰሩ ሰዎች በአብዛኛው በተፋጠነ ሁኔታ ፍርድ ቤት መቅረባቸውንና በሁሉም ክልሎች ፍርድ ቤቶች በምርጫ ወቅት ክፍት ሆነው የሚሰሩ ችሎቶችን በመቋቋማቸው ጉዳያቸው በተፋጠነ ሁኔታ ሲታይ እንደነበረ አረጋግጧል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ በምርጫ ጣቢያ ውስጥ ቅስቀሳ በማድረግ፣ በምርጫ ጣቢያ ሁከት በመፍጠር እና ተመሳሳይ ወንጀሎች በመጠርጠር በአዲስ አበባ ከተማ 12 ሰዎች፣ በአዳማ 2 ሰዎች፣ በባቱ 4 ሰዎች፣ በምንጃር እና ሸንኮራ 1 ሰው፣ በወላይታ ዞን 8 ሰዎች፣ በአሶሳ ከተማ 2 ሰዎች፣ በጅማ ከተማ 2 ሰዎች መታሰራቸውን ኮሚሽኑ ተመልክቷል። ተጠርጣሪዎቹ በእለቱ ፍርድ ቤት ቀርበው የእስር ወይም የገንዘብ ቅጣት እንደተላለፈባቸው፣ ከፊሎቹ በነፃና በዋስ መለቀቃቸውን እና የተወሰኑት ለሌላ ጊዜ መቀጠራቸውን ኮሚሽኑ ተከታትሏል።

በአፋጣኝ ፍትሕ የማግኘት መብትን በማረጋገጥ ረገድ የተጠረጠሩ ሰዎችን በፍጥነት ፍርድ ቤት የማቅረቡና እልባት የመገኘቱ ሂደት ተገቢና አበረታች ነው። በአንጻሩ የተወሰኑት ተከሳሾች የፍርድ ሂደቱ የተቻኮለ እንደነበረ እና እራሳቸውን የመከላከልና በጠበቃ የመወከል እድል እንዳልተሰጣቸው የገለጹ በመሆኑ፣ መሰል ሁኔታዎች እንዳይፈጠሩ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።

"በምርጫው ወቅት ለረብሻ ስጋት ይሆናሉ" በሚል ከሕግ አግባብ ውጪ የታሰሩ ሰዎች እንደነበሩ ኮሚሽኑ ተመልክቷል። ከፖሊስ እና ከፀጥታ አካላት ጋር በተደረገው ውይይት ተጠርጣሪዎቹ የታሰሩት ከምርጫው ጋር ባልተያያዘ ምክንያት እንደሆነ ቢገለጽም፣ በአብዛኛው የምርጫ ሂዳቱን ያሰናክላሉ በሚል ጥርጣሬ  የተያዙ ሰዎች እንደነበሩ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ አብዛኛዎቹ ታሳሪዎች ከምርጫው ቀን አስቀድሞ የተያዙ ሲሆን፣ ከመካከላቸው ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ በእስር ቆይተው ከምርጫው ቀን በኋላ ክስ ሳይመሰረትባቸው, በነጻ እና በዋስ የተለቀቁ ይገኙበታል።

በአዲስ አበባ ከተማ፣ የካ ክፍለ ከተማ 25 ሰዎች፣ በባቱ ከተማ 3 ግለሰቦች፣ በነገሌ ከተማ 2 ሰዎች፣ በቶኬ ኩታዬ ወረዳ 9 ሰዎች፣ በነቀምት ዲጋ ወረዳ 20 ሰዎች፣ በአምቦ ከተማ ቁጥራቸው ያልታወቀ ሰዎች፣ በጅማ ዞን 2 ሰዎች፣ በጭሮ ከተማ 75 ሰዎች፣ በጭሮ ወረዳ 28 ሰዎች፣ በገመቺስ ወረዳ 9 ሰዎች፣ በሂርና 40 ሰዎች፣ በጡሎ ወረዳ 120 ሰዎች ከላይ በተጠቀሰው ሁኔታ ታስረው የነበሩ መሆናቸውን ኮሚሽኑ ተመልክቷል። በአዳማ ከተማ በአባ ገዳ ክፍል ከተማ ፖሊስ ጣቢያ ታስረው የነበሩ 28 የጎዳና ተዳዳሪዎች መካከል ከ 18 ዓመት በታች የሆኑ ሕጻናትና ታዳጊዎች 20 ሲሆኑ፣ ከምርጫው መጠናቀቅ በኋላ መለቀቃቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

## 3. ማስፈራራት እና ማስገደድ

ኮሚሽኑ ክትትል ባደረገባቸው አብዛኛዎቹ አካባቢዎች የኮሚሽኑ ባለሙያዎች ያነጋገሯቸው ነዋሪዎች በተለይ በምርጫው እለት ያለማስፈራራትና ማስገደድ በነፃነት በምርጫው ላይ መሳተፋቸውን ገልጸዋል።

በተወሰኑ በተለይም የገጠር አካባቢዎች መራጮች ዛቻ እና ማስፈራሪያ እንደደረሰባቸው ለኮሚሽኑ ጥቆማዎች ደርሰዋል። በደቡብ ክልል አለታ ወንዶ በጎርድአማ፣ ቢቾ እና አጋራ የገጠር ቀበሌዎች

ህብረተሰቡን "ብልፅግናን ካልመረጣችሁ ፓርቲው ካሸነፈ በኋላ ምንም መብት አይኖራችሁም" በሚል ማስፈራራት እና ዛቻ እንደደረሰባቸው ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

በኦሮሚያ ክልል ጭሮ ከተማ በገጠራማው ቀበሌዎች የሚገኙ የተወሰኑ ሰዎች ለኢሰመኮ እንዳስረዱት በምርጫው የማይሳተፉ ወይም የምርጫ ካርድ ያላወጡ ሰዎች በቀበሌ ሚሊሻ እና ፖሊስ ለእስር እና እንግልት እንደተዳረጉና፣ በምርጫው የተሳተፉት በተፈጠረባቸው ጫናና ባደረባቸው ፍርኃት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በተወሰኑ ቦታዎች ከቀጥተኛ ማስፈራራት ውጪ ዜጎች በነጻነት ድምጻቸውን እንዳይሰጡ እንቅፋት በሚፈጥር መልኩ በተዘዋዋሪና በቀጥታ በመራጮች ላይ የፍርኃት ተጽእኖ የሚፈጥሩ የተለያዩ ድርጊቶች እንደነበሩ ኮሚሽኑ ተመልክቷል፡፡

በአማራ ክልል በደብረ ብርሃን ከተማ እና አካባቢው የምርጫ ክልል፣ በቀበሌ 06 የምርጫ ጣቢያ 03-1-ሀ ላይ የምርጫ ቦርድ ፍቃድ ከተሰጣቸው ሰዎች ውጪ የአካባቢው የመንግስት አመራሮች የራሳቸውን ሰዎች መድበው "አስተባባሪ" ነን በሚል ስም በምርጫ ጣቢያው ውስጥና አካባቢ ሲንቀሳቀሱ፣ መራጮችን ሲያሰልፉ እና ሲያስፈትሹ እንደነበር ኮሚሽኑ ተመልክቷል፡፡ እነዚሁ አመራሮችም በተለይ በእድሜ የገፉ መራጮችን "እናግዛችሁ" በሚል ተከትለው እስከ ሚስጥር ድምጽ መስጫው ቦታ ድረስ አብረዋቸው ይገቡ የነበረ መሆኑን እና አንድ የቀበሌ አመራርም እስከ 15 የሚደርሱ አዛውንትና አካል ጉዳተኞችን "ደግፎ" በመያዝ የሚስጥር ድምጽ መስጫ ቦታ ውስጥ ድረስ ሲገባ የኮሚሽኑ ባለሙያዎች ተመልክተዋል፡፡

በምዕራብ ጎጃም ዞን ደምበጫ ወረዳ የጎድበር ቀበሌ ምርጫ ጣቢያ ላይ የምርጫ ቦርድ ካርድ (ባጅ) የሌላቸው የአካባቢው የቀበሌ አመራሮች በምርጫ ጣቢያው ውስጥ ተቀምጠው ለመራጮች ማንን መምረጥ እንዳለባቸው ትዕዛዝ ሲሰጡ ታይተዋል፡፡ በዚሁ ጣቢያ የነበሩ ሌላ የምርጫ አስፈጻሚም እገዛ ያልጠየቁ መራጮችን ጭምር የሚስጥር ድምጽ መስጫው ድረስ ተከትለው በመግባት "እዚህ ላይ ምልክት አድርጊ" ሲል የኮሚሽኑ ባለሙያዎች ተመልክተዋል፡፡

በተመሳሳይ እገዛ ለማድረግ በሚል ምክንያት የተወሰኑ የምርጫ ጣቢያ አስተባባሪዎች፣ የበጎ ድጋፍ የሚያደርጉ ወጣቶች እና በጥቂት ስፍራዎች ደግሞ የገዢው ፓርቲ ተወካዮች ሰዎች በሚስጥር ድምፅ መስጫው ውስጥ በመግባት መራጮችን ያነጋግሩ እንደነበረ የኮሚሽኑ ባለሙያዎች ተመልክተዋል፡፡ ለምሳሌ በቡታጀራ እና በአፋር ክልል ሰመራ፣ አይሳዒታ፣ ሎጊያ እና ዱፍቲ በነበሩ ምርጫ ጣቢያዎች ምርጫ አስፈፃሚዎች የሚስጥር ስፍራው ድረስ በመግባት እገዛ ሲያደርጉ እንደነበረ እና በቡሌ ሆራ በኤጀርስ ፎራ ቀበሌ 02 ሀ ምርጫ ጣቢያ "በጎ ፍቃደኛ ወጣቶች" በሚል የተሰባሰቡ ሰዎች መካከል አንደኛው በምርጫ ጣቢያ የሚስጥር ድምጽ መስጫ ቦታ በመግባት ለመራጮች ካርዳቸውን ሲሞላ የኮሚሽኑ ባለሙያዎች ተመልክተዋል፡፡

በቢሻን ጉራቻ (ጥቁር ውሃ) ምርጫ ጣቢያዎች መራጮች በቡድን በመምጣት በአንድ ላይ ሆነው ወደ ሚስጥር ድምጽ መስጫ ቦታ ሲገቡና የምርጫ አስተባባሪዎች እና የገዥው ፓርቲ ተወካዮች በሚስጥር ድምጽ መስጫው ቦታ ከመራጮች ጋር አብረው ሲገቡ ታይተዋል፡፡

በቡታጅራ ከተማ የኢሰመኮ ክትትል ቡድን በተገኘባቸው 5 የምርጫ ጣቢያዎች የብልጽግና ፓርቲ አመራሮች እና አባላት የምርጫ ቦርድ ከሰጠው ካርድ (ባጅ) ውጪ የራሳቸውን ካርድ አዘጋጅተው ባልተፈቀደላቸው ስፍራ፤ በመራጮች ሰልፍ ላይ፣ በምርጫ ጣቢያ ውስጥና በዙሪያው በመገኘት መራጮችን ሲያዋክቡ ታይተዋል፡፡ የኮሚሽኑ ባለሙያዎች ያነጋገሯቸው መራጮችም አመራሮቹ

ብልጽግና ፓርቲን እንዲመርጡ ሰዎችን በማደራጀት ወደ ምርጫ ጣቢያ እንዲሄዱ እንዳስገደዷቸው ገልጸዋል፡፡

ኮሚሽኑ ክትትል ባደረገባቸው የተወሰኑ አካባቢዎች ማንነታቸውን የሚገልጽ ካርድ (ባጅ) የሌላቸው እና በምርጫ ጣቢያ መገኘት የሌለባቸው ሰዎች በምርጫ ጣቢያዎቹ ውስጥ እንደነበሩ የኮሚሽኑ ባለሙያዎች ተመልክተዋል፡፡

በቡሌ ሆራ የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ የቀበሌ አመራሮች በብዛት ሲገቡና ሲወጡ የታዩ ሲሆን በአዲስ አበባ በተለያዩ ምርጫ ጣቢያዎች ካርድ (ባጅ) የሌላቸው ሰዎች ሲያስተባብሩ እና በጎ ፈቃደኞች ወጣቶች ሰልፍ ሲያስተባብሩ እና ፍተሻ ሲያደርጉ እንደነበረ የኮሚሽኑ ባለሙያዎች ተመልክተዋል፡፡

በተለይም ከተደራጁ ወጣቶች ጋር በተያያዘ በደቡብ ክልል ሚዛን ተፈሪ ከተማ፣ በአዲስ ከተማ ቀበሌ ህብረት 07 እና 08 ምርጫ ጣቢያ አና በአዲስ አበባ ሾሮ ሜዳ እና ስድስት ኪሎ አካባቢ መራጮችን ያለ ስራቸው ሲፈትሹና አብዛኛዎቹ ወጣቶች ‘ገዢው ፓርቲ ያደራጃቸው ናቸው” በሚል ተፎካካሪ ፓርቲዎች ባነሱት ቅሬታ መሰረት ወጣቶቹ ከምርጫ ጣቢያ እንዲለቀቁ መደረጉን ኮሚሽኑ ተመልክቷል፡፡

ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው የምርጫ አስፈፃሚዎች በአብዛኛው በነፃነት ተግባራቸውን እንደሚያከናውኑ ገልፀዋል፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች ምርጫ አስፈፃሚዎች ላይ ከተለያዩ ወገኖች ጫና እንደነበረ የተጠቀመ ሲሆን ለምሳሌ በደቡብ ክልል ከኮንሶ ምርጫ ክልል አስተባባሪ በተገኘው መረጃ መሰረት የምርጫ አስፈጻሚዎች ላይ ዛቻ እና ማስፈራራያ መፈጸሙን ለመረዳት ተችሏል፡፡ በይርጋ ጨፌ ምርጫ ጣቢያ 02 ከምርጫ ቦርድ ውጪ ሌላ ካርድ (ባጅ) የነበራቸው ተዘዋዋሪ ታዛቢዎች የምርጫ አስፈጻሚዎችን ስራ ላይ ጣልቃ በመግባት ሲያስችግሯቸው እንደነበር ከምርጫ ክልል ኃላፊዎች ገለጻ እና ከምልከታ ለመረዳት ተችሏል፡፡

4. የታዛቢዎችን፣ የሲቪክ ማኅበራት አባላትንና የሚዲያ አካላትን ጥበቃ በሚመለከት

የውጭና አገር ውስጥ ምርጫ ታዛቢዎች እና የሚዲያ አካላት በተለያዩ የምርጫ ክልሎች እና ጣቢያዎች እየተዘዋወሩ ሲታዘቡ እና የምርጫውን ሂደት ሲዘግቡ እንደነበረ ኮሚሽኑ ተመልክቷል፡፡ የክትትል ቡድኑ ክትትል ባደረገባቸው አብዛኛዎቹ አካባቢዎች ያነጋገራቸው የአፍሪካ ሕብረት፣ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ)፣ የኢትዮጵያ ሰራተኞች ማኅበር ኮንፌዴሬሽን (ኢሰማኮ)፣ የመምህራን ማኅበር፣ የሲቪክ ማኅበራት ጥምረት እና የእጩዎች ታዛቢዎች በአብዛኛው በተለያዩ የምርጫ ጣቢያ በመገኘት ሂደቱን ለመታዘብ መቻላቸውን እና ያጋጠማቸው የጎላ ችግር አለመኖሩን አስረድተዋል፡፡

ይሁንና በሀዋሳ የተወሰኑ የምርጫ ጣቢያዎች ጋዜጠኞች ምርጫ ቦርድ ከሰጣቸው ካርድ (ባጅ) በተጨማሪ ደብዳቤ እንዲያቀርቡ በመጠየቃቸው መጉላላት የደረሰባቸው ሲሆን፣ ችግሩ በምርጫ ቦርድ ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት አማካኝነት እልባት ማግኘቱን ኮሚሽኑ ተመልክቷል፡፡ እንዲሁም የኢሰመጉ ታዛቢዎች ከምርጫ ቦርድ ምርጫውን እንዲታዘቡ ካርድ (ባጅ) የተሰጣቸው ቢሆንም፤ በጭሮ 1 ምርጫ ክልል ጣቢያ ውስጥ እንዳይገቡ ሲከለከሉና ሲዋከቡ የኮሚሽኑ ባለሙያዎች ተመልክተዋል፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎችም በታዛቢዎቻቸው ላይ የደረሰ ጫና እንደነበረ ለኮሚሽኑ ገልጸዋል፡፡ የአማራ ዴሞክራሲያዊ ኃይል ንቅናቄ (አዴኃን) በምዕራብ ጎጃም ዞን ይልማና ዴንሳ ወረዳ በሚገኘው የኮቲ

ቀበሌ በተመደቡ የምርጫ ታዛቢዎቹ ላይ ድብደባ መድረሱን ለኮሚሽኑ ገልጿል፡፡ በአማራ ክልል የአብን እና የኢዜማ የምርጫ ታዛቢዎች በራሳቸው እና በቤተሰቦቻቸው ላይ በወረዳ እና ቀበሌ አመራሮች በተፈጸሙ የማስፈራራት ድርጊቶች ምክንያት ካርድ (ባጅ) ለመውሰድ ወይም ምርጫዎችን ለመታዘብ ፈቃደኛ እንዳልሆኑና በዚህም ምክንያት ለማሰማራት ካሰቡት ታዛቢዎች ቁጥር ያነሰ ብዛት ያላቸውን ታዛቢዎች ለማሰማራት መገደዳቸውን ለኮሚሽኑ አስረድተዋል፡፡

## 5. ለመብት ጥሰት ተጋላጭ ለሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች የነበረው ተደራሽነት

ምርጫ ጣቢያዎች ለአካል ጉዳተኞች፣ ለነፍሰጡሮች፣ ለአረጋውያን መራጮች እና ለአቅመ ደካሞች ያላቸውን ተደራሽነት በሚመለከት ኮሚሽኑ ክትትል ካደረገባቸው 404 ምርጫ ጣቢያዎች መካከል 82 (20.2%) አካላዊ ተደራሽነት አልነበራቸውም፡፡

ተደራሽ ያልነበሩት ምርጫ ጣቢያዎች ምቹ ባልሆኑ ስፍራዎች የተመሰረቱ፣ የፍሳሽ ውሃ (ቦይ) መሻገሪያዎች የሌላቸው፣ በዳገታማ ወይም ቁልቁለት ቦታ የተቋቋሙ፣ በጭቃማ ስፍራዎች የሚገኙ፣ በሳር የተሸፈነ መንገድ የነበራቸው እና በአጠቃላይ የሁሉንም ዜጎች ተደራሽነት ባረጋገጠ መልኩ ያልተዘጋጁ እንደነበረ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ኮሚሽኑ ክትትል ባደረገባቸው በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች የምልክት ቋንቋ መግለጫ አይሰጥም ነበር፡፡

ይሁንና በአብዛኛው ምርጫ ጣቢያ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋውያን፣ ሕጻን ለያዙ እናቶች እና ለአቅመ ደካሞች ቅድሚያ ይሰጥ እንደነበረ ለማየት ተችሏል፡፡ በአንዳንድ ስፍራዎች ለሴቶች ቅድምያ የተሰጠ ሲሆን፣ በተለይም በጂንካ ከተማ ከምሽቱ 12:00 ሰዓት በኋላ ሴት መራጮች እንዳይመሽባቸውና በዚሁ ምክንያት ሳይመርጡ እንዳይቀሩ በማሰብ በቅድሚያ እንዲመርጡ ተደርጓል፡፡

ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው ሴት መራጮች በአብዛኛው በነፃነት በምርጫው መሳተፋቸውን ገልፀዋል፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች ለሴት መራጮች ምቹ ያልሆነ ሁኔታ ነበር፡፡ ለምሳሌ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በመንጌ ምርጫ ክልል ካሻፍ ሀ ምርጫ ጣቢያ ወደ ምርጫ ጣቢያው የሚገቡ ሴት መራጮችን ወንድ የምርጫ ጣቢያው አስፈጻሚ አካላዊ ፍተሻ ሲያደርግ እንደነበረ የኮሚሽኑ ባለሙያዎች ተመልክተዋል፡፡

ኮሚሽኑ ክትትል ባደረገባቸው አንዳንድ አካባቢዎች የሀገር ውስጥ ተፈናቃች የነበሩ ቢሆንም ልዩ የምርጫ ጣቢያዎች አልነበሩም፡፡ የኮንሶ ዞን ምርጫ ክልል አስተባባሪ በሰጡት መረጃ በኮንሶ ዞን ለነበሩ "ተፈናቃዮቹ ወደ መደበኛ መኖሪያ ቀበሌዎቻቸው ስለሚመለሱ ምርጫ ጣቢያ ማቋቋም አያስፈልግም" በሚል ምክንያት ባለመቋቋሙ በመመሪያው መሰረት ምርጫው እንዳልተካሄደ ለመረዳት ተችሏል፡፡

የዞኑ አስተዳዳር በተወሰኑ አከባቢዎች ለሚገኙ ተፈናቃዮች ተንቀሳቃሽ የምዝገባ ጣቢያዎችን በማቋቋም በምርጫ እንዲሳተፉ ቢያደርግም በሌሎች ስፍራዎች ለሚገኙት ተፈናቃዮች ተንቀሳቃሽ ጣቢያዎችን እና ቅስቀሳዎችን ሳያዘጋጅ በመቅረቱ በምርጫው ሳይሳተፉ ቀርተዋል፡፡

በሰገን ዞን ለሰገን ገነት ቀበሌ ተብሎ የተከፈተው ተንቀሳቃሽ ምርጫ ጣቢያ ምዝገባ ያካሄደው በሎልቱ ቀበሌ እና በሰገን ከተማ ላይ ቢሆንም፣ የድምጽ መስጫ ሂደቱ የተካሄደው በሰገን ከተማ

ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ለምሳሌ የሰገን ገነት ቀበሌ ተንቀሳቃሽ ምርጫ ጣቢያ 02 ላይ 58 መራጮች ብቻ በመመዝገባቸው የነበረው የመራጭ ቁጥር እጅግ አነስተኛ ነበር፡፡

በሌላ በኩል ለምሳሌ በቤንች ሼኮ ዞን በጃንቹ ቀበሌ ለተፈናቀሉ ዜጎች የፀጥታ ጥበቃ በማድረግ እና ትራንስፖርት በማመቻቸት በሚበረታታ መልኩ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በምርጫው እንዲሳተፉ መደረጉን ኮሚሽኑ ተመልክቷል፡፡

## 6. የፀጥታ አካላት ሚና

ኮሚሽኑ ክትትል ባደረገባቸው በአብዛኛዎቹ አካባቢዎች በተለይም በምርጫው እለት የፀጥታ አካላት ተግባራቶቻቸውን በከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት፣ ሙያዊነት እና ገለልተኛነትን ባከበረ መልኩ ማከናወናቸውን ለመመልከት ተችሏል፡፡ የፖሊስ አባላት ምንም አንኳን በአብዛኛው ስፍራዎች በምርጫ ሕጉ የተቀመጠውን ከምርጫ ጣቢያ በ200 ሜትር ርቀት ገደብ መቆየትን ባይከተሉም፤ የፀጥታ ሁኔታውን ሲያስከብሩ እና ጥበቃ ሲያደርጉ ነበር፡፡ በተመሳሳይም ታጥቀው ከምርጫ ጣቢያ በ500 ሜትር ርቀት ውስጥ እንዳይገኙ የሚከለክለውን ሕግ ለማክበር ጥረት ሲያደርጉ ታይተዋል፡፡

ሆኖም ለምሳሌ በአዳማ በ 2 ምርጫ ጣቢያዎች የታጠቁ የፀጥታ አካላት ከድምጽ መስጫ ቦታ በቅርብ ርቀት ላይ ይታዩ ነበር፡፡ በአፋር ክልል ክትትል በተደረገባቸው ምርጫ ጣቢያዎች የሕግ አስከባሪ አካላት መሳሪያ ታጥቀው ከምርጫ ጣቢያው በቅርብ ርቀት እንደነበሩ ተመልክቷል፡፡

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ መንጌ ምርጫ ክልል እና በአማራ ክልል፣ የታጠቁ የክልሉ ፖሊሶች እና ሚሊሻዎች በምርጫ ጣቢያዎች ግቢዎች እና በምርጫ ድንኳኖች ውስጥ ጭምር እንደነበሩ ኮሚሽኑ ተመልክቷል፡፡ በተለይም በምዕራብ ጎጃም ዞን ደምበጫ ወረዳ የጎድበር ቀበሌ ምርጫ ጣቢያ ላይ 15 የሚሆኑ የታጠቁ የቀበሌ ሚሊሻዎች ከምርጫ ጣቢያው ከ25 እስከ 30 ሜትር ርቀት ላይ እንደነበሩና በምርጫ ጣቢያው የተመደበ የምርጫ አስፈጻሚን አርፍደሃል በሚል ማባረራቸውን፤ እንዲሁም ምርጫውን ለመታዘብ የመጡ ካርድ (ባጅ) ያላቸውን የአብንን አባላት እንዳይገቡ በመከልከል እና በማስፈራራት ሲያባርሩ ታይተዋል፡፡

በደቡብ ክልል፣ በተለይም በኮንሶ በሎልቱ ቀበሌ በጋርጩ ተንቀሳቃሽ ምርጫ ጣብያ 4 የታጠቁ የፀጥታ ኃይሎችን ጨምሮ ከ 20 በላይ የደንብ ልብስ የለበሱ ሰዎች በምርጫ ጣቢያው ውስጥ እንደነበሩ የኮሚሽኑ ባለሙያዎች ተመልክተዋል፡፡

## 7. የፀጥታ ሁኔታን በሚመለከት

አዲስ አበባን ጨምሮ ኮሚሽኑ ክትትል ባደረገባቸው ስፍራዎች ከምርጫው በፊት፣ በምርጫው እለት እና ከምርጫው በኂላ የመከላከያ ሰራዊት፣የፌደራል ፖሊስ እንዲሁም የክልሉ የጸጥታ ኃይሎች መሳሪያ በመታጠቅ እና ተሽከርካሪ ላይ ከባድ መሳሪያ በመያዝ በመኪና በመዘዋወር የጸጥታ ክትትል እና ቅኝት ስራ ሲያከናውኑ ቆይተዋል፡፡

በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ጊጂ ዞን ሰኔ 13 ቀን 2013 ዓ.ም. የምርጫ አስፈጻሚዎች የምርጫ ቁሳቁሶችን ከቡሌ ሆራ ከተማ ወደ ያቤሎ ከተማ አጅበው በሚጓዙበት ወቅት በመንግስት የፀጥታ

ሃይሎች እና በታጠቁ ቡድኖች መካከል በተከፈተ ተኩስ፣ አንድ የፌዴራል ፖሊስ መገደሉን እና አንድ መቁሰሉን ለማወቅ ተችሏል።

በሚኤሶ የምርጫ ክልል ድምጽ የተሰበሰበበትን የምርጫ ኮሮጆዎች አጅበው ወደ ጭሮ ሲመጡ በነበሩ የፌደራል ፖሊስ አባላት ላይ ማንነታቸው ባልታወቀ ሰዎች በተከፈተ ድንገተኛ ተኩስ 2 የፌደራል ፖሊስ አባላት ሕይወታቸው ሲያልፍ 3 ቆስለዋል። በሌላ በኩል ቀደም ሲልም በነበረ ግጭትና የሰላም መደፍረስ ምክንያት የምርጫው እለትም የፀጥታ ስጋት የነበረባቸው ቦታዎች ነበሩ። ለምሳሌ በቡሌ ሆራ ምርጫው በከፍተኛ የፀጥታ ስጋት ውስጥ የነበር በመሆኑ፣ የድምጽ ሳጥኖቹ ከሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ተሰብስበው በከተማው ፖሊስ መምሪያ ግቢ ዉስጥ እንዲያድሩና የድምጽ ቆጠራውም በጥዋቱ እዛው እንዲካሄድ ተደርጓል።

የፀጥታ ስጋት በነበረባቸው አንዳንድ ከተሞች የመንቀሳቀስ ገደቦች ተጥለው እንደነበርና በአንዳንድ ቦታዎች ቀድመው የተገለጹ ባለመሆናቸው በነዋሪዎች ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ አሳድረዋል።

ለምሳሌ በአዳማ የምርጫ ቀን ዋዜማ ምሽትና የምርጫው ቀን በከተማው የሕዝብ ትርንስፖርት አገልግሎት እንቅስቃሴ ተከልክሎ ነበር። በነቀምት ከተማ በምርጫው እለት የትራንስፖርት እንቅስቃሴ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ እና ከቀኑ ከ11:30 ጀምሮ ደግሞ ማንኛውም አይነት እንቅስቃሴ በፀጥታ ኃይሎች ተገድቦ ነበር። በዶዶላ ከምርጫው ቀን በፊት ከ11:00 በኃላ የሰዎችን እና የተሽከርካሪ እንቅስቃሴ ተገድቦ ነበር፣ በባቱ/ዝዋይ ከተማ እና በሻሸመኔ ከተማዎች የሞተር ሳይክል ተሽከርካሪዎች ሙሉ በሙሉ እንዳይንቀሳቀሱ ታግደው ነበር ። በምርጫው እለት በባቱ ከተማ ማንኛውም እንቅስቃሴ ከቀኑ 10:00 ሰዓት ጀምሮና በአሶሳ ከተማ ደግሞ የባለ ሦስት እግር (ባጃጅ) ተሽከርካሪዎች መንቀሳቀስ ተከልክለው ነበር።

በነዚህ ክልከላዎች ምክንያት ሰዎች ለምርጫውም ሆነ ለግል ጉዳይ ለመንቀሳቀስ መቸገራቸውን፣ ለአቅመ ደካማ፣ለአረጋዊያን፣እንዲሁም ለድንገተኛ ታማሚዎች እና ለወላድ ሴቶች ትራንስፖርት ችግር መፍጠሩን ኮሚሽኑ ካነጋገራቸው ነዋሪዎች ተረድቷል።

## 8. ከምርጫ አስተዳደር ጋር የነበረው ሁኔታ

ኮሚሽኑ ክትትል ባደረገባቸው አብዛኛዎቹ አካባቢዎች በምርጫ አስተባባሪዎች በኩል መራጬን ዜጋ ለማስተናገድ የተደረገው ጥረት የሚያበረታታ ቢሆንም ጥቂት በማይባሉ ስፍራዎች መራጮችን ለበርካታ ሰዓታት ያስጠበቁ ረዥም ሰልፎች ስለነበሩ፤ በተወሰኑ ቦታዎች መራጮች በድካምና መሰላቸት ምርጫውን ትተው ሲመለሱ ታይተዋል።

የተፈጠረውን መዘግየት በመገንዘብና መራጬ እንዲስተናገድ በማሰብ ቦርዱ የድምፅ መስጫ ሰዓቱን ማራዘሙ ተገቢ እና ትክክለኛ እርምጃ ቢሆንም፣ የድምጽ መስጫ ሰዓት ስለመራዘሙ ያላወቁ የምርጫ ጣቢያዎች በመዘጋታቸው እና የድምጽ መስጫ ሳጥኖቹን በመቆለፋቸው፣ የተመለሱ መራጮች እንደነበሩ ኮሚሽኑ ተመልክቷል።

**አባሪ፡ ክትትል የተደረገባቸው ስፍራዎችን፣ ምርጫ ክልሎች እና ምርጫ ጣቢያዎች**

| ተ.ቁ | ክልል/ከተማ መስተዳደር | የተሸፈኑ ስፍራዎች[1] | የተሸፈኑ ምርጫ ክልሎች | የተሸፈኑ ምርጫ ጣቢያዎች |
|---|---|---|---|---|
| 1. | አዲስ አበባ | ሁሉም ክፍለ ከተሞች | 12 | 25 |
| 2. | ድሬዳዋ | ድሬዳዋ ከተማ | 2 | 39 |
| 3. | ኦሮሚያ | ቡረዩ፣ ቡሌ ሆራ፣ አምቦ፣ ደንዲ፣ ነቀምት፣ ጭሮ፣ ሰበታ፣ ለገጣፎ፣ ሻሸመኔ፣ ዝዋይ፣ ባሌ ሮቤ፣ ባሌ ጎባ፣ ጅማ አዳማ፣ ዶዶላ፣ ወሊሶ፣ | 27 | 117 |
| 4. | አማራ | ባህርዳር ከተማ፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ ደሴ፣ ደብረ ማርቆስ፣ ጎንደር ደብረ ብርሃን | 15 | 40 |
| 5. | ደቡብ ብ/ብ/ሕ | ሀዋሳ፣ ወላይታ ዞን፣ አርባምንጭ፣ ኮንሶ፣ ጂንካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ዲላ፣ ይርጋጨፌ፣ ሚዛን ተፈሪ፣ ቡታጅራ፣ ወልቂጤ፣ ወራቤ፣ አገና | 24 | 85 |
| 6. | ሲዳማ | ሀዋሳ፣ ቱላ፣ አለታ ወንዶ፣ በሌላ፣ ይርባ | 5 | 26 |
| 7. | አፋር | ሰመራ፣ ዓይሳዒታ፣ ሎጊያ፣ ዱብቲ፣ አዋሽ ሰባት፣ አዋሽ አርባ | 7 | 32 |
| 8. | ቤንሻንጉል ጉምዝ | አሶሳ፣ መንጌ | 4 | 12 |
| 9. | ጋምቤላ | ጋምቤላ ከተማ፣ አቦቦ፣ ጉደሬ | 3 | 28 |
| | | **ጠቅላላ** | **99** | **404** |

[1] ስፍራዎቹ በአብዛኛው መዳረሻ የነበሩ ስፍራዎችን የሚጠቁሙ ሲሆን የክትትል ቡድኖቹ በአቅራቢያ የሚገኙ የገጠር ወረዳዎችን ጨምረው ተመልክተዋል፡፡